# የIGRA ፖዚቲቭ የምርመራ ውጤት ካለዎ

ኖርዌይ ውስጥ የተወሰኑ ቡድኖች በተዳጋጋሚ ለሳንባ ምች በሽታ የIGRA የደም ምርመራ ይደረግላቸዋል።

**የIGRA ምርመራ ፖዚቲቭ ውጤት ምን ትርጉም አለው?**
ፖዚቲቭ የሆነ የIGRA ምርመራ ውጤት ማለት በሳምባ ምች በሽታ ተጠቅተዋል ማለት ነው። ይህ ማለት ህመምተኛ ነዎት ማለት አይደለም። ከአለማችን ሰዎች 1/3ኛ የሚሆኑት በሳምባ ምች በሽታ ባይሰቃዩም ፖዚቲቭ የሆነ የIGRA ምርመራ ውጤት እንዳላቸው ይታመናል። ይኸም ማለት በተደበቀ የሳምባ ምች በሽታ ተጠቅተዋል ማለት ነው።

**የተደበቀ የሳምባ ምች በሽታ አደጋ ያስከትላል?**

የተደበቀ የሳምባ ምች በሽታ ያለበት ሰው በሕይወት ዘመኑ ከሌሎች የበለጠ በበሽታው የመያዝ እድል አለው። በግምት ከ20 ሰው አንዱ ይህ ተሞክሮ ይኖረዋል። በበሽታው በተጠቁ ጊዜ ወይም የሰውነትዎ በሽታን የመከላከል አቅም በሌሎች በሽታዎች (ለምሳሌ በ ኤች አይ ቪ ) ወይም በሕክምና ሂደት (የካንሰር ሕክምና) ምክንያት ጥንካሬውን ካጣ፣ በበሽታው የመያዝ እድልዎ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርሳል፤ የሳንባ ምችን ለማከም የሚያስችሉ ሕክምናዎች አሉ፣ ብዙዎቹ ታማሚዎችም ሙሉ ለሙሉ ይፈወሳሉ።

**ወደ ሌሎች ላስተላልፍ እችላለሁ?**
የድብቅ የሳንባ ምች ተጠቂዎች የበሽታው ታማሚዎች አይደሉም፣ ስለዚህም በሽታውን ወደሌሎች ሊያስተላልፉ አይችሉም።

**ሕክምና ያስፈልገኛል?**
አንዳንድ ጊዜ ምናልባት የሳንባ ምች በሽታው እንዳይዳብር ለማድረግ የመከላከያ ሕክምና ሊያስፈልግ ይችላል። ይህንን የሚወስነው ዶክተርዎ ነው። ይህ አይነቱ ሕክምና በተለይ ለአንዳንድ ግለሰቦች አስፈላጊ ነው፣ ለምሳሌ ለአዲስ ተጠቂዎች፣ ሕጻናት እና በሽታን የመከላከል አቅማቸው ለተዳከመባቸው ሰዎች።

**በተለይ ማወቅ የሚገባኝ ነገር አለ?**
ፖዘቲቭ የሆነ የIGRA ምርመራ ውጤት አለዎ ማለት በማንኛውም መልኩ የአኗኗር ዘይቤዎን መቀየር አለብዎ ማለት አይደለም፤ ነገር ግን በሕመሙ ከተያዙ ለዶክተርዎ የIGRA ፖዘቲቭ/የተደበቀ የሳንባ ምች ውጤት እንዳለዎ በማሳወቅ ለእርስዎ የሚገባውን ሕክምና ማግኘትዎን ማረጋገጥ አለብዎ። ይህ በተለይ አስፈላጊ የሚሆነው የሚከተሉትን የሳንባ ምች ምልክቶች ማሳየት ከጀመሩ ነው:-

- ረጅም ጊዜ የቆየ ሳል (ከ3 ሳምንታት በላይ)
- ረጅም ጊዜ የቆየ ትኩሳት
- የሌሊት ላብ
- የክብደት መቀነስ

**ተጨማሪ መረጃ የት ማግኘት እችላለሁ?**
http://www.fhi.no/tema/tuberkulose/informasjon-til-pasienter